# Learning by Ear 2013

## መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE FIVE: የፍቅር ደብዳቤዎች እና እንባ

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Yann Durand**

**COPY EDITOR: Charlotte Collin**

**List of characters by scene:**

**SCENE 1: MORNING AT ሙሉቱ HOME**

- ምህረት (F, 15)
- ሉሊት (F, 40)

**SCENE 2: ንጉሴ WRITES A LOVE LETTER TO ምህረት**

- ንጉሴ (M, 16)
- አቶ ጃለታ (F, 35)

**SCENE 3: HISTORY LESSON IN ምህረት CLASSROOM**

- GROUP OF STUDENTS (M/F, 15/16)
- ርዕሰ መምህርት ሰብለ (F, 50)
- ምህረት (F, 15)
- ትዕግስት (F, 15)
- ዳንኤል (M, 16)

- **ንጉሴ (F, 16)**

**SCENE 4: ሉሊት GIVES BIRTH TO HER BABY AT HOME**

- **ሉሊት (F, 40)**
- **ሙላቱ (M, 45)**
- **ወይዘሮ ሠዓዳ (F, 65)**

**1. INTRO - NARRATOR:**

**ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ የአፍሪቃ ወጣቶች በሚያጋጥማቸዉ ፈተና ዙሪያ የሚያዉጠነጥነዉን "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" የተሰኘውን ተከታታይ አዲስ ትምህርታዊ ድራማ አምስተኛ ክፍል ይዘን ቀርበናል። ይህ ተከታታይ ድራማ ምህረት፤ ንጉሴ እና ዳንኤል የተሰኙ ሶስት ወጣቶችን የቀን ተቀን ህይወት ይዳስሳል። ሶስቱም እጅግ ጥሩ በተሰኘዉ በቦንጎ አካዳሚ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይማራሉ። ነገር ግን ህይወት ለሶስቱም በተለያየ ሁኔታ ከብዶአቸዋል። እስኪ እስከዛሬ የነበረዉን ሁኔታ እናስታዉስ።**

**ምህረት የድሀ ቤተሰብ ልጅ ናት። ወደ ቦንጎ አካዳሚ የሚያስገባ የነጻ ትምህርት እድልበማግኘቷም ትምህርቷን ጀምራለች፡፡ በአዲሱ ትምህርት ቤቷ በመጀመሪያው የትምህርት ቀን በአንድ ጊዜ በሁለት ወንዶች ተፈላጊ መሆን ምን አይነት ስሜት እንደሚፈጥር ተረድታለች፡፡ሁለቱ ወጣቶች ማለት ንጉሴ እና ዳንኤል እየተከታተሏት ነው!**

2. **ዳንኤል (EP 04, 58 & 68)**:“ **ይቅርታ፣ ምህረት ላነጋግርሽ እችላለሁ… በግል?...(…) ምህረት፣ ወደ ክፍል ልሸኝሽ እችላለሁ? በርግጥ የሚቻል ከሆነ ማለቴ ነዉ ፡፡?"**

3. **ንጉሴ (69):** “ መልካም ሰዓቱ ከደረሰ ጥሩ ነው፡፡ ደግሞ እኔ ብመልሳት የተሻለ ይመስለኛል። አንተ ባቀረብክላት ጥያቄ በእውነት ደስተኛ አይደለችም…

4. **ምህረት (70):** “ሁለታችሁንም አመሰግናለሁ፡፡ ግን ብቻዬን መሄድ እችላለሁ፡፡”

እዚህ ላይ ምህረት ያላወቀችው ነገር ቢኖር አባቷ ጭካኔ የተሞላበት ዕቅድ ማሰናዳታቸውን ነው፡፡ የምህረት እናት አንደገና አርግዘዋል፤ በአንፃሩ የትዳር አጋራቸው ደግሞ አንድ መጥፎ ሀሳብ ፀንሰዋል፡፡

5. **ሙላቱ (EP 04, 37):** “ ህምምም…ይህንን መናገር ባልፈልግም ልጁን ብናስወጣው የተሻለ እንደሆነ አስባለሁ፡፡”

**(KW BEGIN)**

6. **ሉሊት: (39)** “ አይሆንም፣ አይሆንም፣ ምን ማለትህ ነዉ፣ አይሆንም፣ ፈጽሞ አይሆንም! ሙላቱ፣ ያንን ማድረግ አትችልም! አልፈቅድልህምም!“

7. **ሙላቱ**: “ አፍሽን ዝጊ፣ አንቺ የማትረቢ! ምን የማትረባ ሴት ናት! **(Slap on the face)** የዚህ ቤት አባወራ እኔ ነኝ! ወስኛለሁ! እኔ ህግ አወጣለሁ አንቺ ደግሞ ትታዘዣለሽ!”

**(KW END)**

“የፍቅር ደብዳቤዎች እና እንባ” የእዚህታሪክ አምስተኛ ክፍል ርዕስ ነው። እስኪ አሁን በታንዲካ ጎስቋላ መንደር ውስጥ ወደሚገኘው ወደ እነ ምህረት ቤት እናቅና። ታሪኩ የሚጀምረው በማግስቱ ጠዋት ላይ፤የምህረት እናት ወ/ሮ ሉሊት፣ ምጥ ሊጀምራቸዉ ሲል ነው።

**SCENE 1: MORNING AT ሙለቱHOME**

**8. SFX: MORNING ATMO IN SLUM SETTLEMENT**

**9. ምህረት:** እማዬ እንደዚህ አዝነሽ አይቼሽ አላውቅም! ምንድን ነው ነገሩ ፤ ምን እየሆነ ነው?

**10. ሉሊት:** ሀዘን? እኔ? የለም። አላዘንኩም። እኔ …እኔ እእ ደክሞኝ ነው። ታውቂያለሽ- እርግዝናው ያዉዉዉ ።

**11. ምህረት:** ከአባዬ ጋራ በድጋሚ ተጣላችሁ እንዴ?

**12. ሉሊት:** አይ! ለምን እንደዛ ታስቢያለሽ? አልተጣላንም። እኔ እና አባትሽ ፍጹም ሰላም ነን።

**13. ምህረት:** ለመንትያ ወንድሞቼ፣ ለቅዱስ እና ለብሩክ የሆነ ነገር መደረግ አለበት እንዴ?

**14. ሉሊት:** ምህረት፣ እንደዚህ ብዙ ጥያቄዎችን መጠየቅሽን ተይኝ። ወንድሞችሽ ደህና ናቸው።.

15. **ምህረት:** እውነትሽን ነው ግን? እንዴት አወቅሽ፣ እማዬ? ለመጨረሻ ጊዜ ያናገርሻቸው መቼ ነበር? ከአክስቴ ለምለም ጋር ወደ ላቦራያ ከሄዱ ጊዜ ጀምሮ ስለ እነርሱ ምንም እንዳልሰማሁ አውቃለሁ፡፡

16. **ሉሊት:** **(complaining of pain)** አአሀ... ኡኡኡሀ...ምምምሀ...

17. **ምህረት:** **(in panic)** እማዬ ምጥ ነዉ? ፤ ልጁ መጣ? ምን ላድርግ? አባዬን ሄጄ ከስራ ቦታ ልጥራው? ወይስ አዋላጇ ወይዘሮ ሠዓዳን ልጥራቸዉ? የሚኖሩት እዚሀ ቅርብ ነው፡፡

## KW BEGIN

18. **ሉሊት:** **(breathing slowly)** አሁን ማንንም አትጥሪ፡፡ ምንአልባት ምጥ ላይሆን ይችላል፡፡ አባትሽ አሁን ስራውን ጥሎ እንዲመጣ አልፈልግም፣ እቤት ቢመጣ ምንም የሚያደርገው ነገር የለም፡፡ በተጨማሪም የማታ ፈረቃውን አሁን ይጨርሳል፡፡

19. **ምህረት:** ግን እኮ እማዬ፣ ደህና አትመስይም፡፡ ምንም ደህና አትመስዪምም፡፡ ስለዚህ እንዲህ ትቼሽ ትምህርት ቤት መሄድ አልችልም! ልጁ አሁን ለመምጣት ቢወስንስ?

20. **ሉሊት:** (catching her breath from time to time) አትጨነቂ ምህረቴ፣ እስከ ዛሬ ሶስት ጊዜ እኮ ወልጃለሁ! ምንም አልሆንም፤ ይልቅ ተዘጋጂ እና ወደ ትምህርት ቤትሽ ሂጂ፡፡

21. ምህረት: እርግጠኛ ነሽ እማዬ? ወደ ትምህርት ቤት ስሄድ በወ/ሮ ሠዓዳ ቤት በኩል አልፌ መጥተዉ እንድያዩሽ ማድረግ እችላለሁ።

**KW END**

22. ሉሊት: (panting) መልካም፤ እንደዝያ አድርጊ። ግን አሁን ቶሎ ካልወጣሽ ትምህርት ቤት ይረፍድብሻል፤ ግን ለምሳ የሚበቃ ገንዘብ አለሽ?

23. ምህረት: ትንሽ ቆጥቤ ያስቀመጥኩት አለ፤ ስለዚህ ጥቂት ገንዘብ ቀርቶኛል። ቢያንስ ለጥቂት ቀናት ምሳ መብያ ይሆነኛል።

24. ሉሊት: ጎበዝ የኔ ልጅ። ቶሎ ዉጭ፤ በቃ መልካም ቀን።

25. ምህረት: ላንቺም መልካም ቀን ይሁንልሽ እማ። ምንድን ነው...ምንአልባት ምጥ ላይሆን ይችላል እንዳልሽው እንዲሆን እመኛለሁ።

26. SFX DOOR OPENING

27. MUSIC INTERLUDE

## SCENE 2: ንጉሴ WRITES A LOVE LETTER TO ምህረት

28. SFX: PEN SCRIBBLING ON PAPER

29. ንጉሴ: (reading out loud while writing) “ውድ ምህረት። በዚህ ጽሁፌ ላሳውቅሽ የፈለግሁት...” (cuts himself off, frustrated) አሀ! ይሀ ለፕሬዝዳንቱ የሚጻፍ አይነት እንጂ የፍቅር ደብዳቤ አይመስልም!

30. SFX: PAPER BEING CRUMPLED UP AND THROWN

31. **ንጉሴ:** (excited) አውቃለሁ! ኡፍፍፍ፣ ይህንን ለምን ቀደም ብዬ አላሰብኩትም? ኢንተርኔት ዉስጥ,,-እዛ ውስጥ ነው ትክክለኛ ቃላት ማግኘት የምችለው። እርግጠኛ ነኝ ልጠቀምባቸው የምችልባቸው ብዙ የፍቅር ደብዳቤ ናሙናዎች እዚያ ውስጥ መኖር አለባቸው ።

32. **SFX: COMPUTER BEING TURNED ON**

33. **ንጉሴ:** ምህረት፣ የእኔ ልትሆኚ ነው። ያ ደደብ ዳንኤል እድሎቼን እንዲያበላሽ ልፈቅድለት አልፈልግም። ኦህ ምን አይነት ነገር ነዉ! ጊዜው እያለቀብኝ ነው... እንዴ! ምን አይነት ቀርፋፋ ኮምፒዩተር ነዉ አባካችሁ ... እባክህን ፈጠን በል!

34. **SFX: GENTLE KNOCK ON DOOR**

35. **ወይዘሮ ዘውዲቱ:** ንጉሴ፣ ትምህርት ቤት ለመሄድ ተዘጋጅተሀል?

36. **ንጉሴ:** እማ፣ ቆይ ጥቂት ደቂቃ ብቻ ስጪኝ...

37. **SFX: DOOR OPENING**

38. **ንጉሴ:** (very angry) ምንድን ነው፣ እንዴ፣ እማ! ጥቂት ደቂቃ ስጭኝ አልኩሽ አይደል። ለምን አሁንም እንደ ህጻን ትቆጥሪኛለሽ?

39. **ወይዘሮ ዘውዲቱ:** (shocked) ወይ፣ አምላኬ! ንጉሴ፣ ምን እየሰራህ ነበር? ይህ ሁሉ ወረቀት ወለል ላይ ለምን ተዝረከረከ? ኮምፒዩተር ላይ የምትፈልገውስ ምንድን ነው?

40. ንጉሴ: (defensive) ምንም! እማ፣ ግን አሁን ድንበር ጥሰሻል! ይህ የግል ክልል እኮ ነዉ። በዚያ ላይ እኔ...እኔ... ኢንተርኔት ላይ የሆኑ ነገሮችን ለመማር እየሞከርኩ ነበር።.

41. ወይዘሮ ዘውዲቱ: እንደሱ ከሆነ ታድያ፣ አሁን የኮምፒዩተሩን መስኮት ለምን ትሸፍናለህ ? እዝያ ላይ ምን እያደረግህ እንደነበር አሳየኝ!

42. **SFX: COMPUTER SHUT DOWN WITH LOGGING OUT TONE**

43. ንጉሴ: (still defensive) ይህ የእኔ ኮምፒዩተር ስለሆነ የፈለግሁትን ነገር ማድረግ እችላለሁ። 16 ዓመቴ እኮ ነው! ከሁለት አመት በኋላ ደግሞ አዋቂ ጎልማሳ እሆናለሁ።

44. ወይዘሮ ዘውዲቱ:: እንደዚያ ነው? መልካም። አንተ እና አባትህ ከተነጋገራችሁ የቆየ ይመስለኛል፤ አይመስልህም?

45. ንጉሴ: አይመስለኝም። እንደውም እኔ ላይ የምታደርጉትን ስለላ የምታቆሙበት ወሳኝ ጊዜ ይመስለኛል! በቃ... አሁንም የግል ጉዳዩን ለኔ ተይልኝ፤ ፍላጎቴን አክብሪልኝ።

46. ወይዘሮ ዘውዲቱ:: (calming him down) እሺ፣ እሺ፣ አቶ "ትልቁ ልጅ" እየወጣሁልህ ነው፤ ግን ያ ማለት በዚሁ ብቻ አበቃ ማለት እንዳልሆነ ታውቃለህ። በተጨማሪ ክፍልህን ማጽዳትህን መርሳት የለብህም። ኡኡ ,,,አምላኬ ክፍልህ እንዴት ታፍኗል፤ ንጹህ አየር የለዉም ፤ ለመተንፈስ

እንኳ አየር አጠረኝ። ,,,አሁን ቶሎ በል በአምስት ደቂቃ ውስጥ መሄድ አለብን! አምስት ደቂቃ!፣ ንጉሴ! መንገዱ በትራፊክ ከተጨናነቀና ከተዘጋጋ ትምህርት ቤት በሰዓቱ ለመድረስ ይረፍድብሃል፤ ከዛ በኋላ ደግሞ ጥፋቱ ያንተ ይሆናል!

**47. SFX: DOOR CLOSES. FOOTSTEPS WALK AWAY AND FADE**

**48. ንጉሴ:** **(Thinking aloud)** በጣም ጥሩ ...ሁሉ ነገር አልጠፋም። ሁለተኛዉ ዕቅድ ምንም የ፤ ኢንተርኔት ዕርዳታ አያስፈልገኝም።፣ በቃ ንፁህ ስሜቴን እና ሀሳቤን እራሴው መጻፍ ነዉ።,,, አዎ ልክ ነው። ማድረግ ያለብኝ ያንን ነው,,, እ እ, ግን በአምስት ደቂቃ? ህምምም...መልካም፣ እስኪ እናያለን።

**49. SFX: PEN SCRIBBLING ON PAPER**

**50. ንጉሴ:** **(reading while writing)** "የእኔ ውድ ምህረት። ከየት እንደምጀምር አላውቅም። ምን እንደሚሰማኝ ልገልጽልሽ ትክክለኛውን ቃል ስፈልግ ነበር,,,,።"

**51. ROMANTIC MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE 3: BIOLOGY LESSON IN ምህረት CLASSROOM</u>**

**52. SFX: TEXT BOOK PAGES BEING OPENED AT RANDOM**

**53. ATMO CLASS ROOM (PEOPLE SITTING QUIETLY IN A ROOM; SOME CHATTING; PAPER RUSTLING)**

**KW BEGIN**

**54. ርዕሰ መምህርት ሰብለ:** እሺ እንግዲህ እንዳልኩት፣ እኔ-ርዕሰ መምህራችሁ ሰብለ- የባዮሎጂ መምህራችሁ እሆናለሁ፡፡ እናም የሳምንቱን ርዕስ ከመጀመራችን በፊት ሁልጊዜም ተማሪዎቼ ፊታኝ ነገር እንዲጠይቁኝ እፈልጋለሁ፡፡ እውቀት የምር የሚያዝናና ነገር ነው፤ አያችሁ ተመሳሳይ ነገር ለተለያዩ ሰዎች የተለየ ትርጉም ነው ያለው። ስለእዚህ፣ ዛሬ ስለ ዝግመተ ለውጥ ምንነት እንወያያለን። ስለዝግመተ ለውጥ ምን ታስባላችሁ/ ምን ታዉቃላችሁ? እሺ እዚያ ጋር፣ ዳንኤል፣ ቀጥል

**55. ዳንኤል** ዝግመተ ለውጥ እኛ ሁላችን ጭራ እንደነበረን ቀስ በቅስ ግን ከጊዜ ብዛት እንደጠፋ የሚተነትነው ሀሳብ ነው፡፡

**56. SFX: HUGE LAUGHTER FROM CLASS**

**57. ርዕሰ መምህርት ሰብለ:** መልካም፡፡ ጥሩ፣ እሺ እስኪ ገምቱ ? አዎ ዳንኤል ልክ ነው፡፡ ቢያንስ በከፊል ልክ ነው፡፡ ግን ወደእዚያ ሃሳብ በኋላ እንመጣለን፡፡ ሌላ ማን ሊያብራራልኝ ይችላል? ዝግመተ ለውጥ የሚለውን ቃል ስትሰሙ ምን ሃሳብ ይመጣባችኋል? እሺ,,,,,ምህረት…?

**58. ምህረት:** ህይወት በምድር ላይ እንዴት እንደጀመረ የሚያሳይ ሀሳብ ነው፡፡

**59. ርዕሰ መምህርት ሰብለ:** በጣም ጥሩ! በአጠቃላይ ዝግመተ ለውጥ ህይወት በምድር ላይ እንዴት እንደጀመረ የሚያብራራ ሳይንሳዊ መላምት ነው፡፡ የዝግመተ ለውጥ መላምትን የጀመረው ቻርለስ ዳርዊን የሚባል ሳይንቲስት ነው፡፡ ህይወት ያላቸው ነገሮች ሰውንም ጨምሮ ከብዙ ሚሊየን ትውልዶች

በኋላ እየተለወጡ አሁን የምናያቸውን መስለዋል ሲል ተናግሯል፡፡

**60. ምህረት:** ስነፍጥረትስ? በሀይማኖት ግን በምድር ላይ ሁሉንም ነገር እግዚአብሔር እንደፈጠረ ተምረናል፡፡ ስለዚህ ማንን ማመን ነዉ ያለብን?

**61. ርዕሰ መምህርት ሰብለ:** ጥሩ ጥያቄ ነዉ፣ ምህረት! ማንን እንመን? የዝግመተ ለውጥ መላምት እና ስነፍጥረት ለክፍለ ዘመናት ሲጋጩ ኖረዋል፡፡ እውነቱን ለመናገር ማንንን ማመን እንዳለባችሁ መምረጥ የእናንተ ፋንታ ነው፡፡ ያንን ማንም ሊወስንላችሁ አይችልም! በአሁኑ ጊዜ እንደውም ሁለቱ መላምቶች አንዱ ከሌላኛው ሙሉ ለሙሉ የተለየ እንዳልሆነ ብዙ ሰዎች ስለሚያስቡ በዝግመተ ለውጥ ውስጥም የፈጣሪ እጅ እንዳለበት ሊያምኑ ይችላሉ፡፡ ግን ወደ እናንተ ትምህርት ስንመጣ ሁለቱንም መላምቶች ማወቅ አለባችሁ፡፡ ተግባባን? **(SHORT PAUSE, KW END)** እሺ፣ አሁን ሁላችሁም እባካችሁ መጽሐፍታችሁን ክፈቱ፣! ስለ ቻርለስ ዳርዊን የዝግመተ ለውጥ መላምት እንድታነቡ ጥቂት ደቂቃ እሰጣችኋለሁ ፤ ስመለስ የተወሰኑ ጥያቄዎችን ስለምጠይቃችሁ በጥንቃቄ ምንበብ አለባችሁ!

**62. SFX: ርዕሰ መምህርት ሰብለ HIGH HEELS WALKING TO THE DOOR**

**KW END**

**63. ትዕግስት:** **(whispering in excitement)** ምህረት! ምህረት፣ እዚህ ጋር- ይኸውልሽ የሆነ ነገር ይዤልሻለሁ፡፡

**64. ምህረት:** ምንድን ነው እሱ ትዕግስት? ሀሳቤን ሰብስቤ ማንበብ እፈልጋለሁ፡፡

65. ትዕግስት: ይሄንን አታምኝም ,,, ይሄ እኔ ያሰብኩት ነገር የምር ከሆነ ,,,,.

66. ምህረት: እሺ። ቶሎ በይ። ምንድን ነው? ረባሾች ናቸው ብሎ ንጉሴ ለርዕሰ መምህርቷ እንዲነግርብን አንፈልግም።

67. ትዕግስት: እርሱ ይናገርብሻል ብዬ አላስብም።

68. ምህረት: ትዕግስት፣ ምን ለማለት ፈልገሽ ነዉ ግን?

69. ትዕግስት: እንኪ ይህንን በኋላ መጸዳጃ ቤት እስክንሄድ ድረስ ደብቀሽ ያዝዉ እዛ እናየዋለን።

70. SFX: ENVELOPE BEING HANDED OVER

71. ምህረት: ምንድን ነው? ደብዳቤ ? ከማን ነዉ ?

72. ትዕግስት: ቲጂ ዝም ብሎ ደብዳቤ አይደለም፣ ። የፍቅር ደብዳቤ ይመስለኛል!

73. ምህረት: የፍቅር ደብዳቤ?

74. ትዕግስት: ሽሽሽሽ፣ አትጨሂ,,,, አዎ እንደዛ መሰለኝ።

75. ምህረት: ከማን?

76. ትዕግስት: መ-ል-ካ-ም-... ዋናው ቁም ነገር ያ ነው። ደብዳቤውን ዛሬ ጠዋት ንጉሴ ነዉ በሚስጢር የሰጠኝ። የነገረኝም ለአንቺ እና ለአንቺ ብቻ እንድሰጥሽ ነዉ።

77. ምህረት: በኋላ አነበዋለሁ፣

78. ትዕግስት: ወይኔ፣ ወይኔ-ከባድ ችግር ያጋጠመን ይመስለኛል። ዳንኤል ወደ ተቀመጥሽበት እየመጣ ነው።

**79. SFX: ዳንኤል FOOTSTEPS**

**80. ዳንኤል** **(overly cool)** ሀይ፣ ምህረት። የሆነ ነገር አምጥቼልሻለሁ። ይህ ትክክለኛ ጊዜ እንዳልሆነ ባውቅም መቆየት አልቻልኩም። ይሄውልሽ- ወስደሽ ጊዜ ሲኖርሽ ተመልከቺው። እንደምትወጂው ተስፋ አደርጋለሁ።

**81. SFX: ENVELOPE HANDED OVER**

**82. ንጉሴ:** **(shouting)** ዳንኤል፣ ተመልሰህ ቦታህ ላይ ልትቀመጥ ትችላለህ! በዚህ ጉዳይ ላይ ደግሜ መናገር አልፈልግም

**83. ዳንኤልኤል:** **(sarcastic)** ይቻላል፣ አለቃ። የሆነ የሚጠጣ ነገርስ ላምጣልዎ?

**84. SFX: STUDENTS LAUGH UNDER THEIR BREATH**

**85. ትዕግስት:** ምህረት፣ ውቢት! ያጋጠመሽ አስደሳች ችግር ነው። ክፍላችን ውስጥ ካሉ ሁለት አሪፍ ወንዶች ሁለት የፍቅር ደብዳቤዎች! እድለኛ አይደለሽ? **(sighs)** ዉይይ እኔስ አንቺን መሆን ተመኘሁ

**86. ምህረት:** **(sighs too)** እኔ ደግሞ እኔ ባልሆንኩ ኖሮ ብዬ ተመኘሁ።

**87. SFX: MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE 4: ሉሊት GIVES BIRTH TO HER BABY AT HOME</u>**

**88. SFX: SLUMDWELL AMBIENCE**

**89. ሉሊት:** **(in intense labour pains)** ኡ ኡህ ኡህ…ወይኔ!

**90. ወይዘሮ ሠዓዳ:** **(encouraging)** ወ/ሮ ሉሊት፣ ደርሻለሁ! በርቺና ግፊ! ጥሩ ይዘሻል፤ በርቺ፤ ሙላቱም እዚሁ ነዉ፤ ዉጭ እየጠበቀ ነዉ። በርቺ ሁሉም ጥሩ ይሆናል። ግፊ አይዞሽ!

**91. ሉሊት:** **(catching breath)** ኡው ኡውውውው! ሙላ…ቱ ኦኦኦ…አይ…ሆንም። አልቻልኩም። ኧረረረረረረግህ

**92. SFX: SOUND AND CRY OF AN INFANT, CRIES CONTINUE IN BACKGROUND**

**93. SFX: BLANKETS BEING WRAPPED AROUND BABY**

**94. ሉሊት:** **(sighing heavily from relief)**

**95. ወይዘሮ ሠዓዳ:** **(excited)** ወ/ሮ ሉሊት ቆንጆዬ ሴት ልጅ ወለድሽ እል እል እል! ጡት እንድታጠቢያት ህጻኗን ከመስጠቴ በፊት መጀመርያ እትብቷን መቁረጥ ይገባኛል።

**96. SFX: SCISSORS SNAPPING ON SOMETHING. CLEANING OF FLOOR WITH RAG**

**97. ወይዘሮ ሠዓዳ:** እንኳን ደስ አለሽ፣ ወ/ሮ ሉሊት! ይህችት ልጅሽ! አሁን አባትዋ እንዲገባ እና ደስታሽን እንዲጋራ ልንፈቅድለት የምንችል ይመስለኛል።

**98. SFX: TENSE MUSIC**

**99. SFX: BABY SUCKING BREAST MILK**

**100.ሉሊት:** **(begging in tears)** አይሆንም፣ አባክዎን ሙላቱን አያase1ቡት! አባክዎን ወይዘሮ ሠዓዳ እንደሱ አያድርጉ።።ጊዜው አሁን አይደለም።

**101.ወይዘሮ ሠዓዳ:** **(tries to calm ሉሊት)** ሽሽሽ፣ ሉሊት... ብዙ አቅም አባክነሻል፤ ብዙ ደምም ፈስሶሻል። ማረፍ እና እና በደንብ መመገብ አለብሽ። ከዚያ ይሻልሻል። **(calls out)** ሙላቱ! ሙላቱ! ናና ትንሿን ልእልትህን እንኳን ደህና መጣሽ በላት! እኔ አሁን መሄዴ ስለሆነ ሲ.መቸኝ ተመልሼ መጥቼ እጠይቃችኋለሁ።

**102.SFX: IRON SHEET DOOR BEING OPENED**

**103.SFX: FOOTSTEPS APPROACHING**

**104.ወይዘሮ ሠዓዳ:** እንኳን ደስ አለህ ሙላቱ! ሴት ልጅ አግኝተሃል። አሁን እኔ መሄድ አለብኝ ። ደህና ሁኑ። ሙላቱ!ሉሊት እና ልጅህን ተንከባከብ!

**105.SFX: IRON SHEET DOOR BEING CLOSED**

**106.ሙላቱ:** **(slow but strong threatening voice)** ሉሊት፣ ህጻኗን ስጪኝ...

**107. ሉሊት:** እባክህን ያንን አታድርግ። ህጻኗ መጀመሪያ መመገብ ይኖርባታል። ስለዚህ ለእኔ ግዜ ስጠኝ። እባክህን፣ አንድ ወይም ሁለት ...ቀን ብቻ እንድትሰጠኝ እለምንሀለሁ።

**108.ሙላቱ:** አዝናለሁ። አሁኑኑ መውሰድ አለብኝ! አማራጭ የለንም።

**109.SFX: BABY CRYING AS THERE IS A LITTLE FIGHT TO TAKE HER**

**110.ሉሊት:** **(crying uncontrollably)**

**111.ሙላቱ:** **በደንብ አድምጪኝ፡፡ ወይዘሮ ሠዓዳ ወይ ሌላ ሰው ስለ ህጻኗ ቢጠይቅሽ ከተወለደች ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ መሞቷን ንገሪያቸው፡፡ ተሳስተሽ የማደርገውን ነገር ብትነግሪያቸው …እመኚኝ ይቆጭሻል!**

**112.MUSIC INTERLUDE**

**113.OUTRO/MODERATOR:**

**አሁን የተከሰተዉን ነገር ታምናላችሁ? አቶ ሙላቱ ልጁን ለሌላ ሰው ሊሰጥ ነው! ወ/ሮ ሉሊትስ ይህን ሁኔታ እንዴት ይችሉታል? ሉሊትም ከዳንኤል እና ከንጉሴ የፍቅር ደብዳቤዎችን ከተቀበለች በኋላ ሌላ መንታ መንገድ ፊቷ ተጋርጧል፡፡ ስለዳንኤልን የወደፊት እቅድ ማወቅ ከፈለጋችሁ፤ የቪዲዮ ዘገባውን መከታተል ትችላላችሁ። በተጨማሪም በድረ-ገጽ አድራሻችን dw.de/lbe ላይ መከታተል ትችላላችሁ። አስተያየታችሁን በፌስ ቡክ ገጻችን ላይም ልታኖሩልን ትችላላችሁ። ለዛሬ እዚህ ላይ እንሰናበታለን ጤና ይስጥልን።**